# ለተማሪ የተዘጋጀ አመታዊ መመርያና ስለ ገበና "ስለ ብሕትዉነት" አጠባበቅ ማስታወቂያ (Directory Information)

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850
የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የMCPS መመሪያ JOA-RA፣ የተማሪ መረጃ/መዛግብት

**በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ስለ ገበና "ብሕትዉነት" ህግ/ Privacy Act (FERPA)፣ (20 U.S.C.§1232g፤ 34 CFR ክፍል 99) ያለዎትን መብቶች ስለማሳወቅ የተዘጋጀ አመታዊ መመርያ ለማየት ግልባጩን ገጽ ይመልከቱ**

## የማዉጫ/ጠቋሚ መረጃ

ትምህርት ቤቶች የማዉጫ/ጠቋሚ መረጃዎችን ይፋ መዝገብ፣ ሆነር ሮል ሽልማቶች፣ እና ሌሎችንም በጋዜጣ ወይም የሞንትጎሞሪ ሕዝብ ት/ቤቶች (Montgomery County Public Schools (MCPS) ድረ ገጽ ማስታወቂያዎች ለመሳሰሉት ዝርዝሮችን ይሰጣሉ። የተማሪ ስም፣ አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር መረጃ ለማንኛውም ለወላጆች/አሳዳጊዎች ፣ አስተማሪዎች፣ እና የትምህርት ቤት ተማሪዎች ጥምረት ድርጅቶች ይፋ ሊደረግ ይችላል። በእርስዎ በኩል ተቃውሞ ከሌለ በስተቀር፣ ት/ቤቶች መረጃውን ያለርስዎ ፈቃድ ሊያስተላልፉት/ሊገልፁ ይችላሉ።

መምህራን በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ወደፊት እንዲያዩት ቨርቹወል ትምህርቶችን መቅዳት ይችላሉ። የተማሪዎ ምስል እና ድምጽ በእንደዚህ ዓይነት ቀረጻዎች እንዲያዙ የማይፈልጉ ከሆነ እባክዎ ከዚህ በታች ያመልክቱ።

የማዉጫ/ጠቋሚ መረጃዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- የተማሪ እና/ወይም የወላጅ /አሳዳጊ ስም፣ አድራሻ፣ የኢሜይል አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር፤ የተማሪ የትውልድ ቀን፤ የሚያጠናው/የምታጠናው የትምህርት ዓይነት፤ የክፍል ደረጃ፤ በይፋ የሚታወቅ የተለያየ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች ተሳትፎ፤ የተገኙ ድግሪዎች እና ሽልማቶች (ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን ጨምሮ)፤ በቅርብ ጊዜ የተማሩበት ትምህርት ቤት፤ የተከታተሉባቸው ቀናቶች፤ ፎቶ ግራፍ፣ ወይም ሌላ ተመሣሣይ፤ የአትሌቲክ ቡድን አባሎች የሰውነት ክብደት እና ቁመት፤ እና ሌሎችም ተመሳሳይ መረጃ።

ትምህርት ቤትዎ የእርስዎን የማይጎዳ እና ግላዊነትን የማይጋፋ የማውጫ/ጠቋሚ መረጃ እንዲገልጽ ካልፈለጉ፣ ከዚህ በታች ያለውን መረጃ በመሙላት ይህን ማስታወሻ ለትምህርት ቤትዎ እስከ ሰፕቴምበር 11፣ 2023ይመልሱ።

የዚህ ማስታወቂያ ተጨማሪ ቅጅዎች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ት/ቤቶች (MCPS) ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ ፣ እናም በእስፓንሽኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በቬትናሚስ፣ በቻይንኛ፣ በኮሪያኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

ይህ ቅጽ በየአመቱ መሞላት አለበት።

ይህ ቅጽ እስከ አርብ፣ ሰፕቴምበር 11፣ 2023ለትምህርት ቤትዎ ካልተመለሰ፣ማንነትዎን የማይጎዳ የማውጫ/ጠቋሚ መረጃ እንዲሰጥ ይስማማሉ ተብሎ ይወሰዳል።

በሌላ ጊዜ ሀሳብዎን መለወጥ ካስፈለገዎ፣ ትምህርት ቤትዎን በቀጥታ ያግኙ።

ከሰፕቴምበር 11፣ 2023 በኋላ ከተመዘገቡ፣ ይህን ቅጽ በምዝገባ ወቅት ሊሞሉት ይችላሉ

Montgomery County Public Schools
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**ለ2023-2024 የትምህርት ዘመን ግላዊ ጠቋሚ መረጃ እንዳይሰጥ ስለመጠየቅ**

ከሚከተሉት ምድቦች አንዱን ይምረጡ፡-

❑ እባክዎ ማንኛውንም ግላዊ መረጃ እንዳይገልጡ። (ፍቺውን እላይ ተመልከቱ)

❑ እባክዎ የሚከተለውን ጠቋሚ መረጃ ክፍል ወይም ክፍሎች አይስጡ። (በሚመለከተዉ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ)

❑ ስም ❑ የስልክ ቁጥር(ሮች) ❑ ፎተግራፍ ❑ አድራሻ ❑ የትዉልድ ቀን
❑ የኢሜይል አድራሻ(ዎች) ❑ የወላጅ/አስዳጊ ስሞች ❑ የክፍል ደረጃ

እንዳይሰጥ ከተጠየቀዉና እላይ ከተጠቀሰው በስተቀር፡-

❑ ለማናቸውም የትምህርት ቤት ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ እና ተማሪዎች የጋራ ድርጅቶች ይፋ ይደረግ
❑ ለ Honor Roll /ለሆነር ሮል ህትመት/መጽሔት ይፋ ❑ ይደረግለአመታዊ-መጽሀፍ/yearbook ፎቶ ይሰጥ

❑ በተመሳሳይ ክፍል ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ወደፊት እንዲያዩት የተማሪዬ ምስል እና ድምጽ በቨርቹወል ትምህርቶች ቅጅ ዉስጥ እንዳይካተት።

የተማሪ ስም ______________________ ክፍል______ የመታወቂያ ቁጥር______________

ትምህርት ቤት ______________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ፣ የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ ፊርማ ______________________ ቀን____/____/_____

ስለ ልጅዎ የተወሰኑ መረጃዎችን እንዳይሰጡ ካልገደቡ በስተቀር፣ እያንዳንዱ ግላዊ መረጃ በተሰጠ ቁጥር የወላጅ ፈቃድ ሳይጠይቁ የየእለት የስራ ክንውኖችን እና ተለምዷዊ/መደበኛ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ለትምህርት ቤት ስርአት እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች አዎንታ እየሰጡ ነው።

## በ FERPA *መብቶችዎን ስለማሳወቅ የተገለጸ አመታዊ ማስታወቂያ

የሞንትጎሞሪ ካዉንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን፣ የልጅዎን የትምህርት መረጃዎች በተመለከተ በ (በቤተሰብ ትምህርታዊ እና ግላዊ መብቶች ህግ) Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)፣ አግባብነት ባላቸው የፌደራል ደንቦች እና በሜሪላንድ ህግጋት Code of Maryland Regulations (COMAR) 13A.08.02 መሠረት የተወሰኑ መብቶች አለዎት። እነዚህ መብቶች ከዚህ በታች በአጭሩ የተገለጹ ሲሆን በዚህኛው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደምብ ላይ ይበልጥ ተብራርተዋልRegulation JOA-RA, Student Records/የተማሪ መዛግብትwww.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/joara.pdf

1. የተማሪ መዝገቦች ግምገማ። የልጅዎን የትምህርት መዝገቦች ትምህርት ቤቱ የእርስዎን የጽሁፍ ጥያቄ ካገኘ 45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመመርመር እና የመገምገም መብት አለዎት። ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የጽሁፍ ጥያቄ በደረሳቸው በ10 ቀናት ውስጥ፤ የተማሪው/ዋን መለያ፣ ግምገማ ወይም ከምደባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ስብሰባዎች ከመደረጉ አስቀድሞ እንዲያከናውኑ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS ግብ ነው። ትምህርት ቤቱ የልጅዎን መረጃዎች የሚያገኙበትን እና መዝገቦችን የሚያዩበትን ጊዜ እና ቦታ በማመቻቸት ያሳውቅዎታል። በዚህ ግምገማ ወቅት ርእሰ መምህሩ/ሯ/ ወይም ተወካይ ይኖራሉ።

2. የተማሪ መዝገቦች ማሻሻያ። የልጅዎ መዝገቦች ትክክል እንዳልሆኑ፣ እንደሚያሳስቱ፣ ወይም የልጅዎን ግላዊነት መብቶች እንደሚጻረሩ ካመኑ፣ ትምህርት ቤቱ መዝገቦችን እንዲያሻሽል የጽሁፍ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዎት። MCPS Regulation JOA-RA፣ የተማሪ ፋይሎች-Student Records፣እነዚህን ዋና ዋና ጥያቄዎች የመመለስ አሠራር ሥርአት፣ እንደአስፈላጊነቱ የማህበረሰብ ሃሳብን መግለጽ ጭምር። በዚህ ደንብ መሰረት ውጤቶች ለድርድር አይቀርቡም።

የተማሪ መዝገቦች መግለጫ። በፌደራል ወይም የስቴት ህግ ያለፈቃድ እንዲገለጽ በተለይ የተፈቀደ እስካልሆነ ድረስ፣ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS በግለሰብ ደረጃ የሚታይ መረጃ ከልጅዎ የትምህርት ዘገባዎች ይፋ ከመደረጉ በፊት የፅሁፍ ፈቃድ የመስጠት መብት አለዎት። ስለ መረጃ አሰጣጥ መመርያዎች፣ እንዲሁም መረጃ እንዳይገለጽ ያለመስማማት ሁኔታን የሚገልጽ በዚህ ፎርም በስተጀርባ ተጠቅሰዋል። በተጨማሪ፣ ለመገንዘብ የሚያስፈልግዎት ነገር፤ ህጋዊ የትምህርታዊ ሃላፊነት ላላቸው፣ ** የትምህርት ቤት የስራ ሃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ መምህራን፣ ወይም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS ለተቀጠሩ ሰራተኞች (መረጃ) ለመግለጽ ስምምነት እንደማያስፈልግ ያስተውሉ፣ እንደዚሁም የሚከተሉትን ሌሎች ስለ MCPS የሚሰሩ የስራ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት መረጃ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ጨምሮ፦ በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ሠራተኞች፣ እና የጤና ባለሙያዎች፣ የት/ቤት የጥበቃ ሠራተኞች፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አባል፣ (Montgomery County Board of Education member)፣ ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ወይም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ሕዝብ ት/ቤቶች MCPS እንዲሰሩ ኮንትራት የተቀጠሩ ካልሆነም የሞንትጎሞሪ የሕዝብ ት/ቤቶች የራሱን ቅጥር ሠራተኞች (ዓቃቤ ሕግ፣ ወይም ኦዲተሮች)፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ሌላ በፈቃደኝነት ሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች በኮሚቴ የሚያገለግል ወይም ሌሎች በትምህርት ዘርፍ በመርዳት የሚያገለግሉ።

- ጥያቄ ከቀረበ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS የትምህርት መረጃዎችን፣ ለሌሎች ት/ቤቶች፣ ለትምህርት ዲስትሪክት፣ ወይም ከሁለተኛ ከረጃ በላይ ላሉ የትምህርት ተቋማት፣ የተማሪዉ/ዋ መረጃ የተፈለገው ለትምህርት ምዝገባ ወይም ወደ ሌላ ት/ቤት፣ የትምህርት ዲስትሪክት (ክፍለከተማ)፣ ወይም ሌላ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመዛወር ከሆነ ያለ ፈቃድ መረጃ መስጠት ይችላል። በተጨማሪ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS በህጋዊ መንገድ ከተማሪ መዝገቦች ላይ ግለሰብን ገላጭ የሆኑ መረጃዎችን፣ ከእርስዎ የቅድሚያ የጽሁፍ ስምምነት ውጭ፣ የተለዩ መንግስታዊ ድርጅቶችን፣ የጸደቁ የምርምር ፕሮጀክቶችን፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝን ወይም ህጋዊ የፍርድ ቤት መጥሪያን፣ ወይም የጤና ወይም የደህንነት ድንገተኛ አደጋን ጨምሮ በFERPA ለተፈቀዱ ለሌሎች ምክንያቶች ሊገልጽ ይችላል።
- ተጨማሪ መረጃ በMCPS ድረ-ገጽ ወይም በእርስዎ የአካባቢ ትምህርት ቤት በሚገኘው የMCPS መመሪያ JOA-RA፣ የተማሪ መዝገቦች ይገኛል።

3. አቤቱታ ለዩ.ኤስ. የትምህርት መምርያ በFERPA ያሉዎት መብቶች እንደተጣሱ ካመኑ እና ሁኔታውን/ጉዳዩን በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች MCPS የይግባኝ ደረጃዎች ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች አጥጋቢ ካልሆኑ፣ በዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ የቤተሰብ ፖሊሲ አፈጻጸም ጽ/ቤት (the Family Policy Compliance Office)፣ 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-5920 ወይም በ1-800-USA-LEARN (1-800-872-5327) በመደወል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት።

* ብቃት ያላቸው ተማሪዎች መብቶች። እላይ የተገለጹት መብቶች 18 አመት ለሆነ/ች ወይም ድህረ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋም በመካፈል ላይ ላለ/ች ተማሪ ይተላለፋል/ይሰራል፤ ነገር ግን፣ የሚያሟሉ (የወላጅ) ጥገኛ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚያሟላው/የምታሟላው ተማሪ የቅድሚያ ስምምነት ሳያስፈልጋቸው የልጃቸውን መረጃ/መዝገቦች ማግኘት/ማየት ይችላሉ።

** የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ሙያዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የትምህርት መረጃዎችን/መዝገብን ለማየት/ለመገምገም ካስፈለጋቸው አጠቃላይ ህጋዊ የትምህርት ሙያ ሃላፊነት አላቸው።